# እጅግም ስለት! ይቀዳል አፎት!



## ከአደራ ምህዋር መውጣት፤
## የብቻ-እብጠት፤ ለቅስፈት

የፖለቲካ “ኢሴንትሪክ”
እኔ ብቻ ነኝ ልክ!
የአውቅልሃለሁ እልክ!
ዞሮ-ዞሮ ለመንበርከክ።

“ዘመነኛ-አጉራ-ዘለል”፤
አዲስ-ቄንጥ፤አዲስ-አምል”።

ከኀቦ ዉ.ቃው
ማኒቶባ ካናዳ
ጥቅምት 16/2000

የዘመናት ሲቃ ሰቆቃው
. . .መጠን የለሽ በደሉ
ረመጡ ልኩን ሲያልፍ
መቃጠል መብሰልሰሉ፤
የክተት አዋጅ አወጁ. . .
የነፃነት ያለህ! አሉ፤
በፈፋ፤በገደሉ፤
በምስራቅ፤በምራብ
በከተማ፤በገጠሩ
ያ ሁሉ ሰራዊት ተሞ
ሊመለስ አልነበረም. . .
በረከትን አ-ስ-ታ-ሞ
መለስንም ተ-ሳ-ል-ሞ፤

ሰማዩም ሲከብድ
ዶሮ ሁለቴ ሳይጮህ
“ነጋ-ተበየና”
“በየነ-ነጋና”
አሉን እንዲመለስ
ስለቱን ወደ አፎት
ቁ-ር-ጥ! የጀግና እንዥርት!
ፍ-ሥ-ሥ! የዥግና አሞት!
እጥፍ-ድርብ ክደት!
የባንድነት ፅልመት።

እስከ አፍጢሙ የሞላውን
ሽምጥ ጋላቢውን
ፀረ-ጎሰኛ ትንግርት
የነፃንቱን ባቡር
ሃዲዱን፤ ስብር! እንክት!
ያንን እቶን!፤ያንን ግለት
ቀዝቃዛ ዉሃ ቸለሱበት
አምኖ ጆሮ ቢሰጣቸው
ከነጭ ከነጫጭባ መክረው
ለመለስ አ-ደ-ሉ-በ-ት!፤
ለሆዳቸው አ-ደ-ሩ-በ-ት።

አገር ከዳር-እዳር ተነቃንቆ
ጨዋታው በድል ተጠናቆ
ወያኔም ተጨናንቆ
አልሞት ባይ ስልጣን አንቆ
ሊወድቅ ተነቃንቆ
-እያለ-
<u>ቀጥ-አረጉን ባንድ ፊሽካ</u>
የስራችሁን ይስጣቹ. . .
. . .ወያኔም ልቡ ረካ
ከእጅ የገባውን ሲሳይ
አስነጠቁን ባደባባይ!
ዋይ ለእነሱ ነው ዋይ!
እኛስ ትምርት ወስደናል. . .
ለዳግመኛው ጉድጉአድ ምሰናል
ወያኔን አምኖ ድርድር
የቁም-ሞት፤የቁም ቀብር!!

ዛዲያ ለያማ!
በየነስ ምን አጠፋ
ፓርላማ ቢያናፋ
መራራስ ምን አጠፋ
በህዝብ ስም ቢያገነፋ
ከፓርላማ መግባቱ
መደርደር ከልደቱ።

አብይ የዲሞክራሲ ጥያቄው
ጉድለት ስለነበረው
ስምንቱ ቅድመ-ሁኔታ
የፃፈው፤የከተበው
ፅላቴ ነው ያለው
ቁልፍ በመሆኑ ነው።

ግን ህዳእጣን አንገራገሩ
ከበረከት ጋር ተዳሩ
ገብተዉም ተሰነቀሩ፤

የነፃይነቱ መነሻ
ከዋናው ግብ መዳረሻ
አደረጉት እጅ መንሻ
አለበሱት ጥቀርሻ።

ታዲያማ!
    ህዝብ ያለው!. . .
    ጥገናዊ-ለውጥ እምቢዮ
    የክህደት መለዮ
    ባዶ ቡራ ከረዮ
    በወያኔ ግፍ በግኖ
    ከቅንጅት-ህብረት ተግኖ
    አህዛብ አንድ ሆኖ
    ግፈኛው የአድዋ ፋኖ
    እንዲቀር ነበር ተኖ
    እንዲጠፋ ነበር በኖ።

    ይሄ ሆኖ እውነት ሃቁ
    ምንድር ነው ማለቅለቁ?
    በህዝብ ትግል መሳልቁ!።

አዬ!
    የፖለቲካ ስልጠና
    ወኔ ሀሞትን ሸጦ
    አዲስ የመጣ ተስቦ
    ሃሞተ-ቢስ ተሰብስቦ
    የክህደት ካባ ደርቦ
    ነበቦ!-ነበቦ!
    ባዶ ሃይሎጋ ሸቦ።

የማስተዋልም ዳፍንት
የማመዛዘን ዳፍንት
“ልብ-ወለድ ድርሰት”
<u>“ሆድ-ወለድ ድርሰት”</u>
የምራጭም ምራጭ
ጤና የማይሆን
የዳመና ግላጭ

እዚም ዘጭ! እዚያም ዘጭ!
ውሃ ቢወቅጡት እምቦጭ
ቋብ አይገባ ቀላዋጭ
የበረከት ግርፍ!
የጥፋት ምላጭ!።

በምን ቋውንቋ በምን ሂሳብ?
በምን ሳይንስ በምን ጥበብ?
ከእባብ እንቁላል እርግብ?
መለስን አምኖ እንሰብሰብ!
ከበረከት ጋር እንደርብ!።

እሱማ ባህል ሆኖአል!
ይሁንታውን ሳያገኙ. . .
. . .ከፓርላማ መንጠልጠል
ለራስ ምቾት መደላድል፤
ለነጭ ዳረጎታ
ለመለስ የውጭ እይታ
በቃን! ብለናል በቃን
ዘመነኛ በቀቀን
አቻ አምናም ዘንድሮ. . .
. . .አንድ ዘፈን መዝፈን
ደግሞ ደጋግሞ ማላዘን።

“ቀን የሰጠው ቅል” አደሙ
“እንፅጌም ጎምዡ አለሙ
ልደቱ ና ሙሼ ሰሙ
እንደ ከርሞው ልያጦዙት
ለቦለቲካ ሰጥ-አገባ
ደመ-ወዝ ሊቆጥሩበት
በጎሰኝነት ግርሻ
በጎጠኝነት ፋሻ
ሊጀቡኑት፤ሊያጅሉት።
ሌላ አምስት የግፍ ዓመት
መቼ ነበር የህዝብ ምኞት?።

ስለወያኔ ክፋት
ዲያቢሎስ፤መሰሪነት
ከዬህ በላይ ማስረገጫ. . .
ምን ትንተና? የምን ትምርት
ምን ተአምር?የምን ትንግርት?

. . .ወይስ ተፅፅታቹ
ከግፈኛው ፓርላማ
. . .ዘው ስለአላቹ?

ዛዲያማ!
የአሰፋ ማሩ ህልፍት
መች ብሎናል ክህደት
የሽብሬ ደሳለኝስ
ኖሩአል ለመለሳለስ?

“የምተማመንበት ካራ
ጉበት ላይ ሲደርስ ፈራ”
ሆነብን እና ነገሩ
ሩቅ አውርተው ቅርብ አደሩ
“ዘመሚት” ሁነዋልሳ. . .!
አስወሰዱን “በወሳንሳ”. . .!!

ጥቂቶች ተመራርጠው
በአፈ-ሙዝ አስገድደው
ሰላሙን አደፍርሰው
ፓርላማ ተወዝተው
ፓርላማ ተጎልተው
ሆዳቸውን ሞሉ እንጂ!. . .
. . .ለወገኔ ምን ተረፈው?።

የእልፍኝ ቦለቲካ
ቁብ የለው በረካ
እንዲያው እንካ-በንካ፤
መቸ ለህዝብ አበለጡ?
ሁሉም ለራሳቸው አበጡ

ባደባባይ ያወሩትን. . .
በቀትር የለፈፉትን. . .
. . .ግና ሳይመሽ ሸመጠጡ
አለሁህ ያሉት ሁሉ. . .
ከዚያው ተዱለው ቀለጡ።
ምነው ብናስተውል በቅጡ?

የፕሮፌሰር አስራት ህልፈት
የፀጋዬ-የአበራሽ፤የተጋድሎ ገድል. . .
የአስፋ ማሩ መስዋእት
የሺብሬ ደሳለኝ አደራ
ከአርነት በመለስ. . .
ሎሚ ተራ! ሎሚ ተራ!
ነበር! ወንበር ልንጋራ?
ወይስ
እርስ-በርስ ልንማዘዝ ካራ?
ለምን ታጋቡኛላቹ ግራ?

"እድሜ ለነፅጌ! "-እድሜ-ለነመዋ!"
"ተኩሰው ላይመቱ፤
ተሙአግተው ላይረቱ፤
የጫካዉን አውሬ፤
ቀሰቀሱት ከንቱ"
መለሰም ተረተ. . .
. . .ሞላለት ስለቱ።

ከኢዲሊም ቀስተ-ደመና አልፎ
ከመኢአድ ኢዴፓ ባሻገር
ፀረ-ወያኔ ሁላ. . .
. . .ሳይሰባሰብ ባንድ እድር
ካልታሰበ ለወገን፤ ካልታሰበ ለአገር
ዉሃ ቅዳ፤ዉሃ መልስ. . .
መከለስ፤መከላለስ. . .
የቀን ህልም፤የቀን ቅዥት
ሞኝነት? ባንድነት?፤ባንድነት?ሞኝነት።

ቸር ይግጠመን